جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

# ማን እንደፈጠረዎ? ለምንስ እንደፈጠረዎ? እና ከሞት በኋላ ምን እንደሚኖር ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ?

هَلْ سَأَلْتَ نَفْسَكَ؟ مَنْ خَلَقَكَ؟ وَلِمَاذَا؟ وَمَاذَا بَعْدَ المَوْتِ؟

አማርኛ

أمهري

የተለያዩ ኢስላማዊ ይዘቶችን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች
አገልግሎት ማኅበር የሊቃውንት ኮሚቴ

# هَلْ سَأَلْتَ نَفْسَكَ؟ مَنْ خَلَقَكَ؟ وَلِمَاذَا؟

# وَمَاذَا بَعْدَ المَوْتِ؟

# ማን እንደፈጠረዎ? ለምንስ እንደፈጠረዎ? እና ከሞት በኋላ ምን እንደሚኖር ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ?


اللَّجْنَةُ العِلْمِيَّةُ

بِجَمْعِيَّةِ خِدْمَةِ المُحْتَوَى الإِسْلَامِيِّ بِاللُّغَاتِ

የተለያዩ ኢስላማዊ ይዘቶችን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማኅበር የሊቃውንት ኮሚቴ

بِسْمِ اللهِ الرَّحَمَنِ الرَّحِيمِ

# ማን እንደፈጠረዎ? ለምንስ እንደፈጠረዎ? እና ከሞት በኋላ ምን እንደሚኖር ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ?

አንተ የሰው ልጅ ሆይ! ማን ፈጠረህ? ሰውነትህን በአጉሊ መነፅር (ማይክሮስኮፕ) ብትመለከት የረቀቀ ጥበብና ተዓምር ዓለም ታያለህ። በሰውነትህ ውስጥ ያለች እያንዳንዷ ሕዋስ (ሴል) በውስጧ ውስብስብ የሆኑ የዘረመል ኮዶችን ትይዛለች። እነዚህን ኮዶች ማን እንደጻፋቸው፤ በትክክለኛው በታቸውስ ማን እንዳስቀመጣቸው እራስህን ጠይቀህ ታውቃለህ?

እያንዳንዱ ግዙፍ ህንጻም ይሁን ደሳሳ ጎጆ የሰሪውን ታሪክ ይናገራሉ። ታዲያ ይህ ሰፊው ዓለም (ዩኒቨርስ) በውበቱ፣ በረቀቀ አሰራሩና ፍፁም የተስተካከለ ስርአቱ ያለ ሰሪ ሊገኝ ይችላል ብሎ ማሰብ ይቻላል?!

አንተ ሰው ሆይ! አንድ ዘመናዊ ስልክ (ስማርት ፎን) ያለ ንድፍ አውጪና ያለ ሰሪ በድንገት ተገኘ ቢባል ወይም ደግሞ ውስብስብ የሆነ የኔትዎርክ መረብ (ሲስተም) ያለ ፕሮግራመር (አዘጋጅ) ወይም

ተቆጣጣሪ ተናቦና በትክክል ይሰራል ቢባል አዕምሮህ እንደማይቀበለው ሁሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ ይህ ታላቅ ፍጥረተ ዓለም በውስጡ ባለው የተቀናጀ ሥርዓት፤ አስደናቂ አፈጣጠር፤ ረቂቅ ህግጋትና ፍጹም በሆነ አደረጃጀት ያለ ፈጣሪ ተገኘ ቢባል አዕምሮ እንዴት ሊቀበለው ይችላል?!

በዚህ ዓለም (ከውን) ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ቅንጣት ከትንሿ አቶም አንስቶ እስከ ትልቁ የከዋክብት ስብስብ (ጋላክሲ) ድረስ የፈጣሪውን ታላቅነትና ኃያልነት ያመለክታል። ይህ ፍጹም ጥበብ የተሞላበት ረቂቅ ሥርዓት ያለሰሪ በባዶ እንዲሁ የተከሰተ እንደሆነ ማሰብ ከአዕምሮ አንጻር ፈጽሞ የማይታሰብና ውድቅ ነው። ጤናማ አዕምሮ ይህ ዓለም ከምንም (ከባዶ) እንደተገኘ ወይም ይህ አስደናቂና ውስብስብ የሆነ የፈጣሪ ጥበብ የአጋጣሚ የዕውር ድንገት ውጤት እንደሆነ ፍጹም ሊቀበል አይችልም!

የሰው ልጅ ትክክለኛ አዕምሮውና ጤናማ ተፈጥሮው ለዚች አለም ፈጣሪ እንዳላት የሚያመላክቱት እንደሆኑት ሁሉ፤ በተመሳሳይ

መልኩ የዚህን ፈጣሪ ባህሪያትና በእኛ ላይ ያለውን መብት (ሀቅ) እንድናስተነትን ይገፋፋናል።

የዚህን ፈጣሪ ባህሪያት ማስተንተን፤ እርሱ ፍጹም በሆነ ምሉእነት የሚገለፅና ከማንኛውም ጉድለት የፀዳ መሆኑን በጥልቀት እንድንገነዘብ በሮችን ይከፍትልናል።

ይህም ማለት ፈጣሪ በውበትና በታላቅነት ባህርያት ሁሉ የሚገለፅ እንደሆነ ያስረዳናል። እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ፤ ሁሉንም አዋቂ፤ በእያንዳንዱ ፍጥረቱና ውሳኔው ላይ ጥበበኛ ነው። ይህ ፍፁምነቱም ሊሆን ይችላል በሚል ጥርጣሬ የምናስበው ሳይሆን አእምሯችን ሳያመነታ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ባህርያቶቹ ላይ የትኛውም ነውር ቢኖርበት ኖሮ በአፈጣጠሩም ይሁን በአስተናባሪነቱ ላይ ክፍተትን ይፈጥር ነበር። ይህ ደግሞ ከምናየው አለም ተጨባጭ ጋር የሚጋጭ ጉዳይ ነው።

ከነውር የፀዳ መሆኑም ማንንም የማይሻ ከፍጡራኑ የተብቃቃ መሆኑንና ይልቁንም ሁሉም ለህልውናቸውና ለመኖራቸው ከእርሱ ከጃይ እንደሆኑ የሚያስፈርድ ነው። ጥራት ይገባውና እርሱ

ከልጅም ይሁን ከባላንጣ የጠራ ነው። ምክንያቱም ልጅም ይሁን ባላንጣ ከእንከን መገለጫዎች መካከል ናቸውና። ልዕለ ኃያሉ አላህ ደሞ ከዚህ የጠራ ነው።

እንግዲያውስ አላህ ፍጹም በሆኑ የታላቅነትና የምሉእነት ባህሪያት የተገለጸ ታላቁ ፈጣሪ እርሱ እስከሆነ ድረስ እኛንም ይሁን ፍጥረተ አለሙን ከምንም የፈጠረ እርሱ ነው፤ በውስጡ ላለውም ሁሉ ባለቤቱ እርሱ ነው፤ ሲሳዩን የሚለግሰንም በእዝነቱ የሚያካብበንም እርሱ ነው፤ ሁሉንም የሚያስተናብርና ሁሉንም የሚያስኬደውም እርሱ ነው፤ ታድያ ለርሱ ተገቢውን ሹክር ልናደርስለት፣ ውዴታውን እንዴት እንደምናተርፍና ከኛ የሚጠበቅብን ሐቁን እንዴት መወጣት እንዳለብን ማጥናት እንዲሁም የተፈጠርንበትን አላማ ለማሳካት ጥረት ልናደርግ አይገንባምን?!

እንዲሁ ፈጥሮን ከኛ የሚጠበቅብን ምንድ ነው? ለምንስ እዚሁ አስገኘን? በህይወት የመኖራችን አላማው ምንድን ነው? ከሞት በኋላስ የሚገጥመን ምንድን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች ሳይነግረን ይተወናል ተብሎ ይታሰባልን?

እስኪ እናስተውል እንበልና የሆነ ሰው እጅግ ድንቅ ህንፃ ሰርቶ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎችን ቢያሟላለትና ከዛም ፅድት አድርጎ ካጠናቀቀ በኋላም ያለምንም ምክንያት እንዲሁ ድንገት ህንፃውን ሙሉ በሙሉ ማፍረሱን ቢጀምር ይህ ሰው ጥበበኛ ልንለው እንችላለንን? እንዲህ አይነቱ ድርጊት ለጤነኛ ሰው የማይገባ ከንቱ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑ ግልፅ ጉዳይ አይደለምን?!

ይህ አይነቱ ድርጊት ለሰው ልጅ እንኳ የማይመጥን ድርጊት ከሆነ ጥበበኛና ውስጥ አዋቂ የሆነው አሏህ ይህንን አለም ፍፁም በተሟላና እጅግ በሚደንቅ ሁኔታ ከፈጠረው በኋላ ያለምንም አላማና ያለምንም ጥበብ መልሶ ያወድመዋል ተብሎ እንዴት ይታሰባል?!

በእውነቱ አሏህ የሰው ልጅን ለላቀ ጥበብ ፈጥሮታል። ይሀውም እርሱን በብቸኝነት ያለምንም ተጋሪ ማምለክ ነው። የፈጠራቸውም በዚች አለም ሊፈትናቸውና በእለት ቂያማ ደሞ እንደየስራቸው ሊተሳሰባቸው መመለሻን አድርጎላቸው ነው። በአላህ አምኖ ለጥሪውም ምላሽ የሰጠ በውስጧ ዘውታሪ

የሚሆንባት የጀነት ፀጋ አለችለት። ከእውነታው ያፈነገጠ ግን የእሳት ጓድ ይሆናል።

አምልኮ እርሱን በብቸኝነት ማምለክ የህልውናችን አላማ በመሆኗ በኛ ላይ ግዴታ የሆነች መብቱ ነች። የምስጋናችንና በአላህ ጌታነት እና በአምላክነቱ የማመናችን ዋነኛዋ ምልክትም እርሷው ነች።

ፈጥሮ በመስማትና በመመልከት ያከበረዎ፤ ተቆጥሮ በማይዘለቅ ፀጋ ያንበሸበሸዎ ጥራት የተገባውና የላቀው አሏህ መሆኑን ያስተውሉ። የደም ስሮ ደምን የሚያዘዋውረው፤ ውሃና እስትንፋስን የሚለግስዎ፤ እዝነትና እንክብካቤው ባይኖር አቅምዎ ምክክ ብሎ ሊጠፋ በሚችልበት ልክ እርሱ ያስፈልጎታል። እንደውም ጥራት ይገባውና ገና በእናትህ ማህፀን ውስጥ ሳለህ ለራስህ እንኳ አንዳች ነገርም ማድረግ በማትችልበት ጊዜ የሲሳይህን ጉዳይ ዋስትናውን ያረጋገጠልህ ነው።

እና ይህ ታላቅ ፈጣሪ እርሶ እንደፈለጉ ሳይሆን እርሱ እንደፈለገው ሊያመልኩት አይገባውምን?! አስተውል እስኪ ለእናትህ ስጦታ መስጠትን ብታስብ ላንተ የሚያስደስትህን ነው የምትመርጠው ወይስ በሚመቻት መልኩ እርሷን ለማስደሰት ስትል እርሷ

የምትፈልገውን ትመርጣለህ? ልክ እንደዚሁ አላህን ማምለክም እኛ እንደፈለግነው ወይም እንደወረስነው ባህል ሊሆን አይገባም፤ ይልቁንም ጥራት ይገባውና እርሱ እንደፈለገውና እኛን ባዘዘበት መልኩ ሊሆን ይገባዋል።

አምልኮ ጥርት ባለ መልኩ ያለምንም ተጋሪ ለላቀው አሏህ ልትሆን ይገባል። በመሆኑም የሰው ልጅ አምልኮውን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ ሊሰጥ ስለማይፈቀድለት ዘልአለሙን እሳት ውስጥ ዘውታሪ የሚያደርገው ወንጀል በአላህ ማጋራት ሆነ። ይህም የሰው ልጅ ከአላህ ጋር ፍጡራኑን ማምለኩ ነው። ጣኦትን፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን ማምለክ ወይም ሰውን ወይም እንሰሳን ደግ ሰውንም ቢሆን ማምለክ ነው። ይህ ሁሉ ደሞ ከሽርክና ከክህደት አይነቶች ነው። በዚህ ላይ ሆኖ የሞተ ሰውም ምንዳው ዘልአለሙን ጀሀነም ውስጥ መዘውተር ነው።

በህይወት የመኖራችንን አስፈላጊነትና ዱኒያ ላይ መገኘታችን አላማው ምን እንደሆነ ሊያሳውቀን ዘንድ አላህ በርካታ ነቢያቶችና መልዕክተኞችን ልኳል። የሁሉም መልዕክተኞች መልዕክት አንዷት ነች፤ እሷም የእስልምና ጥሪ የሆነችው ፈጣሪን ብቻ

ያለምንም ተጋሪ በብቸኝነቱ ማምለክ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ቀደምት መልዕክተኞች ይዘውት የመጡትን መልዕክት የሚያዛቡና የሚለውጡ ሰዎችም አሉ። አላህም የመልዕክተኞች መደምደሚያ የሆኑትን ሙሐመድን ልኮ ለሰው ልጆች የመጨረሻ የሆነውን መልዕክት ሰጣቸው። ይሀውም የተከበረው ቁርአን ነው። ቁርአን የአላህ ቃል መሆኑንና ለመዛባትና ለመለወጥ ያልተጋለጠው ብቸኛው መጽሐፍ መሆኑን የሚያረጋግጡ አእምሯዊም ሳይንሳዊም ማስረጃዎች አሉ። አላህም ከእስልምና ውጭ ሃይማኖትን ከሰው ልጅ ተቀባይነት እንደሌለውና የመልዕክተኞችም ተልዕኮ አንዲት እንደነበረች: እሷም ፈጣሪን በብቸኝነት ያለምንም ተጋሪ እንዲመለከ ማምለክ ጥሪ ማድረግ እንደሆነ በቁርአን ነግሮናል። ለምእመናን የሚሆን ጀነትና ፀጋ እንደተዘጋጀ፤ እንዲሁም እስልምናን አልቀበልም ላለና ከአላህ ውጭ ላመለከ የሚሆን አሳማሚ የእሳት ቅጣት መዘጋጀቱንም ነግሮናል።

እስልምናን ከሌላው ሃይማኖት ለየት ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል ታማኝ የእውቀት ምንጮች ላይ ተመርኩዞው ለእምነታቸው

አእምሯዊም ይሁን ሳይንሳዊ እውነታዎችን በማቅረብ ብቸኛ የሆኑት ሙስሊሞች መሆናቸው ነው። ይህውም እምነታቸው ዛሬ እነሱ ዘንድ እጃቸው ላይ የሚገኘው ከመዛባትም ከመለወጥም የተጠበቀ የሆነው የተከበረው ቁርአን ጥራት የተገባው የፈጣሪያችን አላህ ቃል መሆኑ ነው።

የተከበረው ቁርአን አላህ በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ላይ ያወረደው መጽሐፍ ነው። አላህ በዚህ ባወረደው መጽሐፍ መላውንም ባይሆን አንዲት ምዕራፉን የመሰለች እንኳ አምሳያውን እንዲያመጡ መላው የሰው ዘርን ከአስራ አራት ክፍለ ዘመናት በላይ ለሆነ ጊዜ ተገዳድሮጳበታል። ሰዎች ግን ተሳናቸው። በፍፁም ቋንቋዊ አጠቃቀሙም ይሁን በተአምራዊነቱ እንዲሁም በድንጋጌው አምሳያውን ማምጣት የሚችል ካለ መገዳደሩ አሁንም እንዳለ ነው። ይሁን እንጂ ለዚህ ሁሉ ክፈለ ዘመን አንዳችም ቁርአኑን የሚመስል ነገር ቀርቶ የሚቀራረበውን እንኳ ማምጣት የቻለ አንድም የለም። የቁርአን ተአምራዊነቱ ድካ የደረሰ ፍፁምነት ባለው ቋንቋዊ አጠቃቀሙ ብቻም ሳይሆን እንደውም የፈጣሪ ቃል መሆኑን በሚያረጋግጥበት ልክ አእምሯዊም

ሳይንሳዊም ማስረጃዎችን አጠቃልሎ እስከሚያዝ ድረስ የዘለቀ ነው። ታድያ የተከበረው ቁርአን የፈጣሪ ቃል መሆኑን በሚያረጋግጡ ግልፅ ማስረጃዎች የተሞላ እስከሆነ ድረስ ሊሰጠው የሚገባው አእምሯዊና አመክንዮአዊ ግብረ መልሱ - ዝግጅታቸው ላይ በሰው ልጅ ተፅዕኖ በተደረገባቸው ሌሎች መጽሐፍቶች ምትክ- ቁርአንን ማመንና ይዞት የመጣውን መከተል መሆን አለበት።

ጤናማ አስተሳሰብ ፍጥረተ አለሙን ካልነበረበት ያስገኘና ስርአቱንም ፍፁም የተሟላ ያደረገ የሆነው ፈጣሪ ቃሉ እውነትን በማወቅ ረገድ እጅግ ታማኙ ምንጬ መሆኑን ይረዳል። ታድያ በቁርአን ይህንን በቋንቋም ይሁን በሳይንሳዊ እውነታዎች እንዲሁም ፍፁም በሆኑ ድንጋጌዎቹ ይህንን ያህል ተአምራዊነትን ከማግኘታችን ባሻገር ለዚህ ሁሉ ዘመናት ከመዛባት ተጠብቆ ባየን ጊዜ የአላህ ቃል መሆኑን አምኖ ከመቀበል ውጭ መፈናፈኛ አይኖረንም።

አለፍ ሲልም በቁርአን በመጣው ማመን የእምነት ምርጫ ብቻ ሳይሆን እውነትን ተረድቶ

ከምክንያታዊነት ጋር በሚሄድ መልኩ አእምሯዊ እረፍትም ጭምር ነው።

ጥራት የተገባውና የላቀው አሏህ በተከበረው ቁርአኑ እርሱን ልናመልከው እንጂ ለከንቱ እንዳልፈጠረን በግልፅ ነግሮናል።

ይህችው የምንኖርባት የዱኒያ ህይወት በቅርቡ የምትቋጭ መሸጋገሪያ አለም እንጅ ትክክለኛዋ ዘልአለማዊ ህይወት ምእመናን ጀነት ገብተው ከሃዲያን ደሞ ጀሀነም በሚገቡበት ጊዜ መሆኑን አላህ በቁርአኑ ነግሮናል።

ያ ያለአንዳች ነገር የፈጠረን አላህ ከሞትን በኃላ ወደ ህይወት ሊመልሰን ቻይ መሆኑ ምንም የማያጠራጥር ጉዳይ ነው። በዙርያችን ባለው ፍጥረተ አለም ላይም ተጨባጭ የሆኑ የአምላክ ሁሉን ቻይነት ሙታን ላይ ህይወት እንደሚዘራባቸው የሚያሳዩ ምልክቶችን እንመለከታለን። ሁሉንም ቻይ የሆነው አምላካችን አሏህ አረንጓዴ ከሆነ ዛፍ እሳትን እንደሚያወጣው፤ ከደረቀው መሬት አዝርእትና ጥራጥሬን እንደሚያፈራው፤ ሽልን በእናቱ ሆድ ውስጥ ከፍትወት ጠብታ እንደሚፈጥረው ሁሉ እርሱ

ጥራት ይገባውና በእለተ ትንሳኤ ሙታንን ህያው አድርጎ ከቀብራቸውም ቀስቅሶ ሊመነዳቸውም ቻይ ነው። በዳይም ተበዳይም ስራቸውን ሳይተሳሰቡ ምንዳቸውንም ሳያገኙ ህይወታቸው ይጠናቀቃል ማለት ግፍ ነው።

አንዳንድ ሰው ታድያ እንዲህ ሊጠይቅ ይችላል: እኮ ለምን እስልምና ብቻ? ሌላው ሃይማኖትስ ለምን አይሆንም?

የሰውን ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው ትልቁ ነገር አእምሮ ነው። የአእምሮ ኃላፊነቱም እውነትን መፈለግና ማስተንተን ነው።

የእስልምና ሃይማኖት ከጤናማ አእምሮና ከተስተካከለ ተፈጥሮ ጋር የሚገጥም በመሆኑ የህልውና ጥያቄ ለሆኑ መሰረታዊ የሰው ልጅ ጥያቄዎች አመክንዮአዊ ምላሾችን ይሰጣል። ለምን እዚህ ተገኘን? የህይወታችን አላማ ምንድን ነው? ከሞት በኋላስ መመለሻችን ወዴት ነው?

እስልምና ፈጣሪን ብቻ በአምልኮ መነጠልና ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ እንደሌለ መመስከር ላይ የተመሰረተ ነው። የመጀመርያው የመስክርነት ቃልም ይህ ነው። ላ ኢላሃ ኢለሏህ ብሎ

መመስከር በእስልምና የእምነቱ ምሰሶ ነው። ትርጉሙም ከአላህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው እንደሌለ መመስከር ነው።

ይህች የምስክርነት ቃልም የሚከተሉትን አጠቃልላለች:

ተውሒድ: ማለትም ልጅም ይሁን ብጤ ሳይኖረው ያለምንም ተጋሪ ብቻውን ለአምልኮ የተገባ በሆነ አምላክ ማመን ነው።

ከሽርክ መጥራት: ማለትም ጣኦታትንና ሰዎች በራሳቸው የፈጠሯቸው የሆኑ አምላኮችን ማውገዝ (መካድ) ነው።

እስልምና በመልዕክተኞች ሁሉ ማመንን ግዴታ የሚያደርግ ስለሆነ አላህ በቁርአን በተናገረው መሰረት ዒሳም የአላህ ባርያና መልዕክተኛው ናቸው እንጂ የፈጣሪ ልጅ እንዳልሆኑ ሙስሊሞች ያምናሉ። ምክንያቱም ፈጣሪ ሚስትንም ይሁን ልጅን ከመያዝ የላቀ ኃያል ነው። አላህ ከልጅና ከሚስትም ይሁን ከየትኛውም ነገር የተብቃቃ ነው። በእውነቱ አላህም በቁርአን እንደነገረን ዒሳ ህዝቡ ያለምንም ተጋሪ አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ጥሪ ሊያደርግ ዘንድ በርካታ ተአምራት ከአላህ ተሰጥቶት የተላከ

ነቢይ ነው። ዒሳ በሰዎች ሊመለክ ሳይፈልግ ጭራሽ እሱ ራሱ ፈጣሪውን ሲያመልክ እንደነበር ነግሮናል። አምላክ በሚወድልህ መልኩ ስለ ዒሳ በትክክለኛ እውነታው ልታምን ከፈለግክ ራሱ ወደ እስልምና መግባት ይጠበቅብሃል።

ዒሳ ራሱ ህዝቡን ያዘዛቸው አምላክን በብቸኝነት እንዲያመልኩ እንደሆነ ቁርአን ነግሮናል።

እንደው ጤነኛ አእምሮ ላለው ሰው እንደሱ የሚራብና የሚጠማ ሞትንም ይሁን ክፋትን ከራሱ ላይ መመከት የማይችል አምሳያው የሆነን ፍጡር ማምለኩ አመክንዮአዊ ነውን? የሰው ልጅ ሆይ! ምግብና መጠጥ የሚያስፈልገውና በፀሎትም ወደ ጌታው የሚመለስ የሆነውን የመርየምን ልጅ ዒሳን እንዴት ታመልካለህ? አምላክ ለራሱ ነው የሚፀልየው ማለትስ ለአእምሮ አሳማኝ ነውን? አምላክ በታላቅነት የሚገለፅ፣ በፍፁምነቱ ብቸኛ የሆነ፣ ከአምሳያና ብጤ የጠራ፣ በፍጥረተ አለሙ ውስጥ ያለውም ሁሉ በችሎታውና በስልጣኑ ስር ያደረ አይደለምን?! የሰማያትና የምድር ፈጣሪ እንደ ህፃን ሆኖ ሊወለድ ወረደና ከዛም ፍጡራኑ እንዲገድሉት ራሱን አሳልፎ ሰጠ ተብሎ እንዴት

ይታሰባል?! የሚሰቀሉትና የሚገደሉትኮ ጠፊ የሆኑ ፍጥረታቱ ናቸው። ፈጣሪማ የማይሞት ህያው፤ እንቅልፍና ማንገላጀት እንኳ የሌለበት ራሱን ቻይ 'ኮ ነው። ከታላቅነቱና ከልቅናው ምሉእነት አንፃር ከእንዲህ አይነቱ ጉዳይ የጠራ ሊሆን አይገባውምን?!

አላህ በቁርአኑ እንደነገረን መልዕክተኞች ሁሉ የመጡት አንድ መልዕክት ብቻ ይዘው ይሀውም አጠር ባለ መልኩ ህዝባቸውን አላህን በብቸኝነትና ያለምን ተጋሪ ወደማምለክ ጥሪ ሊያደርጉ ነው። ይሁን እንጂ በጊዜ ሂደት አንዳንድ ሰዎች ይህንን ዘውታሪ መልዕክት አዛቡት። ነቢያቶች ይዘውት የመጡትን የተውሒድ ብርሃን አጠፉት። አላህም የመጨረሻ መልዕክተኛው ሙሐመድን ﷺ ልኮ ከሱ በፊት የነበሩ መልዕክተኞች ሁሉ ይዘውት የመጡትን የተውሒድን ተልዕኮ ሊያድስ ዘንድ የተከበረውን ቁርአን በርሳቸው ላይ አወረደ።

## በመጨረሻም እንላለን ውድ የሰው ልጅ ሆይ:

እስልምና የአዕምሮና የንጹሕ ተፈጥሮ (ፊጥራ) ሃይማኖት ነው። እርሱም ታላቁ ፈጣሪ ለመላው የሰው ዘር የደነገገው ብቸኛው ሃይማኖት ነው፤ ስለዚህ እያንዳንዱ አስተዋይ ሰው አላህን በጌትነቱ፣

እስልምናን በሃይማኖትነቱ፣ ሙሐመድንም በመልክተኝነቱ አምኖ ወደ እስልምና ለመግባት መሽቀዳደም አለበት። ይህም ሰው ምርጫ የሌለው ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም አላህ በትንሣኤ ቀን ለመልክተኞቹ ምን ምላሽ እንደሰጠ ይጠይቀዋልና፤ አማኝ ከሆነ ታላቅ ድልና ስኬት አለው፤ ከሀዲ ከሆነ ደግሞ ግልጽ የሆነ ኪሳራ አለበት።

በዚህች ምድር እውነተኛ ደስታንና በመጨረሻው ዓለም (አኺራ) ስኬትን የምትፈልግ ከሆነ በሕይወትህ ውስጥ ልትወስነው የምትችለው ከሁሉ የላቀ ውሳኔ ወደ እስልምና መግባት መሆኑን እወቅ። በአንተ ላይ የሚጠበቀው ይህችን ቃል ከልብ በሆነ እውነተኛ እምነት መናገር ብቻ ነው፡- "አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢለሏህ፣ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ" (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ)። ከዚያም ሃይማኖትህን መማርና ሁለቱ ምስክርነቶች (ሸሃደተይን) የሚያስገድዱትን በአላህና በመልክተኛው ማመን እንዲሁም የእስልምናን ማዕዘናት ተግባራዊ ማድረግ ጀምር።

አሁኑኑ በላት፤ አታመንታ፤ ሞት በድንገት ሊመጣ ይችላልና። እንዲህ ያለ ትልቅ ቦታ ያለውን ውሳኔ አታዘግይ። ሰይጣን ከበጎ ነገር ሊያዘገይህ ዕድል አትስጠው። ደፋር ሁን፤ ወደ ብርሃንና ቅን መንገድ የሚወስደውን ጉዞህን ጀምር።

ውሳኔህን አሁኑኑ ወስን! እርካታና መረጋጋት የሞላበትን አዲስ ሕይወት ጀምር።

"አሽሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወአሽሃዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ" (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ).

❋❋❋

جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

ይህ መጽሐፍ የሕልውናንና የፍጥረትን ጥያቄዎች ይዳስሳል። ፍጹም ጥበብና ምሉዕነት ያለው ፈጣሪ መኖሩን በምክንያታዊነት ያስረግጣል። በተጨማሪም የሕይወት ዋና ዓላማ አላህን ብቻ መገዛት እንደሆነና ኢስላምም : ብቸኛው : እውነተኛና : (ከመበረዝ) የተጠበቀ : ሃይማኖት መሆኑን ያብራራል። በአላህ መልእክተኛ በሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም ፡ በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲያምኑና ትምህርቶቻቸውንም እንዲከተሉ ጥሪ ያቀርባል። ከሽርክ (በአላህ ላይ ከማጋራት) ያስጠነቅቃል፤ በመጨረሻው _ ዓለምም - (በአኺራ) ፣ ምርመራና / ምንዳ : መኖሩን ያረጋግጣል።